# ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)

## 28 ኛ ሳምንት

### ትንሣኤ

**ዓላማ**

❖ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ መማር፡፡

**ምንባብ**

❖ ማቴ 28፣1-8 ዮሐ. 20፣19-28

**መግቢያ**

❖ በዛሬው ትምህርታችንም ጌታችን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ የተገለጠበትን ታሪክ እንማራለን፡፡

**ትምህርቱ**

❖ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም በክብር ሲገባ ያዩት የአይሁድ መሪዎች ቀንተው በሐሰት ከሠሱት፡፡

❖ሕዝቡን አሳድመውም አርብ እለት በመስቀል ላይ ሠቀሉት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሎ ምሕረት አደረገላቸው፡፡በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላም፤ ተቀበረ፡፡

❖በሦስተኛው ቀን እሁድም ከሙታን ተነሣ፡፡በዚያው ቀንም በመቃብሩ ሽቶ ሊያርከፈክፉ የሄዱ ሴቶች ነበሩ፡፡

❖ነገር ግን ድንጋዩ ከመቃብሩ ተንከባሎ ነጫጭ የለበሱ መላእክት በድንጋዩ ተቀምጠ ተመለከቱ፡፡ ይሄን ሲያዩ የፈሩትን ሴቶች ***ተነሥቶአልና በዚህ የለም የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ***፡ማቴ.28÷5-6 አላቸው፡፡

❖እነርሱም ከመቃብሩ ሥፍራ ደስ እያላቸው ሄዱ፣ለሌሎችም ይሄን ታላቅ ዜና ሊያበስሩ ሮጡ፡፡

❖በተዘጋ በር ተሰብስበው በሩ ሳይከፈት ጌታችን በመካላቸው ሆኖ ***"ሰላም ለእናንተ ይሁን"*** አላቸው፡፡ ከተነሣ በኋላ ሲያዩት የመጀመሪያቸው ነበርና በጣም ተደሠቱ፡፡

❖ከሐዋርያት አንዱ ቶማስም በዚያ አልነበረምና ጌታችን ከሙታን መነሳቱን ሲነግሩት ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ካላገባሁ አላምንም አለ፡፡

❖ከስምንት ቀንም በኋላ ቶማስ ባለበት በአንድ ላይ ተሰብስበው ሳሉ ዳግመኛ ተገለጠላቸው፡፡

❖ቶማስንም ***"ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን"*** አለው፡፡ዮሐ.20፣27 በጎንና በእጆቹ ያለውን ችንካር በመዳሰስም አመነ፡፡***"ጌታዬ አምላኬም"*** አለ፡፡

**ጥያቄ**

1) የአይሁድ መሪዎች ክርስቶስን በሐሰት የከሠሱት ለምንድነው?
2) ጌታችን የተነሣው መቼ ነው?
3) ክርስቶስ እንደተነሣ ለሴቶቹ የነገራቸው ማነው?
4) ክርስቶስ በተዘጋ በር የተገለጠው ለማን ነው?
5) መጀመሪያ ሲገለጥ ያልነበረው ሐዋርያ ማነው?
6) ምን አለ? ጌታችንስ ምን አድርጎ አስተማረው?

**መዝሙር**

አማን በአማን (4)

ተነሥአ እምነ ሙታን (4)

# The Resurrection



ይቆየን።